በስደት የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር አባላት አስተባባሪ ኮሚቴ
Coordinating Committee of Exiled Members of Ethiopian Teachers' Association

*የተሰጠ መግለጫ*

*ጥቅምት 5 ቀን 2008ዓ.ም*

***አክቶበር 5 የዓለም መምህራን ቀን***
***የኢትዮጵያ መምህራን ዕለቱን ያሰቡት በሰቀቀን!***

*አገሮች ስለመምህራንና የትምህርት ጉዳይ እያነሱ መነጋገር ከጀመሩበት ወቅት የኦክቶበር 5/1966 በፈረንሳይ -ፓሪስ ከተማ የተካሄደው ኮንፍረንስ በታሪካዊነቱ የሚጠቀስ ነው። ከዚያ ወቅት በኋላ ቆየት ብሎ ኦክቶበር 5 ቀን 1994 የመጀመሪያው የዓለም መምህራን ቀን ተመሰረተ።ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በያመቱ መምህራንና ማህበሮቻቸውን በመዘከር ኦክቶበር 5 የዓለም መምህራን ቀን በመባል ይታወሳል። ከዚሁ ጋር ተያይዞ የማስተማር ሙያ ክብርና ተቀባይነት እንዲያገኝ በኦክቶበር 12/ 1997 በ29ነኛው የተባበሩት መንግስታት የትምህርት ፣ የሳይንስና ባሕል ድርጅት (UNESCO) ጠቅላላ ጉባኤ ( ኮንፍረንስ) ሲከፈት በታደሙት የዚሁ ድርጅትና የዓለም ሰራተኞች ማህበር ( ILO= International Labor Organization) ተወካዮች ስምምነት ላይ ተደርሶ በፊርማ ጸድቋል። የመምህራን ቀን በዓለም አቀፍ ደረጃ የማህበሩ ዓላማና ፋይዳው መምህራን ለቀጣዩ ትውልድ መሰረታዊ ፍላጎቶችና ፣ ባጠቃላይ ለህብረተሰቡ ዕድገት አጥጋቢ ውጤት እንዲያስመዘግቡ ለመርዳት ነው። ስለሆነም ዩኔስኮ የዓለም መምህራን ቀን የመከበር ግንዘቤ የሚላከው መምህራን ለትምህርትና ለሁለንተናዊ ዕድገት በሚያበረክቱት ፍሬያማ ተግባር ከመሆኑ አንፃር እንደሆነ ያምናል።*

*ሌላው በዓለም ዙሪያ ያሉ የትምህርት ሙያተኞችን ያቀፈው ድርጅት ትምህርት ዓለም አቀፍ (EI- Educational International) የዓለም መምህራን ቀን ኦክቶበር 5 በዓለም አቀፍ ደረጃ ዕውቅና እንዲያገኝና የሕዝብ በዓል ( Public Holiday) ሆኖ እንዲከበር በጽኑ ያምናል። ይህ ግዙፍ ድርጅት ማለትም ትምህርት ዓለም አቀፍ (EI) በተጨማሪ በ1966 እና 1997 የተላለፉ የዩኔስኮ ውሳኔዎች እንደገና ተመርምረው በሁሉም አገሮች ተግባራዊ እንዲሆኑም ያለውን ዕምነት እያራመደ ነው። በአሁኑ ጊዜ ከ100 በሚበልጡ አገሮች የዓለም መምህራን ቀን ይታወሳል። ትምህርት ዓለም አቀፍ (EI) እና በድርጅቱ የታቀፉ 390 እህት ማህበራት በሚያደርጉት እንቅስቃሴ የማስተማር ሙያን ዕውቅና ለማረጋገጥ ዘመቻው እንደቀጠለ ይታወቃል።*

*የሠራተኛ ማህበራት ወይም ሌሎች የሙያ ድርጅቶች መምህራንን በመወከል የዓለም መምህራንን ቀን በተለያዩ ሁኔታዎች በብዙ አገሮች ያከብሩታል።ዕለቱን ከሚያከብሩት ድርጅቶች ፡-*

- *የአውስትራሊያ ትምህርት ሕብረት*
- *የካናዳ መምህራን ፌዴሬሽን*
- *በካናዳ አንታሪዮ የ1ኛ ደረጃ ት/ቤት መምህራን ፌዴሬሽን*
- *በሕንድ የሁሉም 2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች መምህራን ፌዴሬሽን*
- *የጃፓን መምህራን ሕብረት*
- *የኒውዝላንድ መምህራን ካውንስል*
- *ብሔራዊ የመምህራን ህብረት ( ዩናይትድ ኪንግደም ፤እንግሊዝ)*
- *ብሔራዊ የትምህርት ህብረት (ዩ-ኤስ-ኤ አሜሪካ) ይገኙበታል።*

*ትምህርት ዓለም አቀፍ (EI) የዓለም መምህራንን ቀን ሲያከብር በየዓመቱ መሪ መፈክር ያወጣል።የዘንድሮው መሪ መፈክር “ **የሕብረተሰቡን ቀጣይነት በጥሩ መሰረት ላይ ለማቆም መምህራንን በብቃት ማደራጀት**” የሚል ነው።*

ከላይ ስለዩኔስኮ ፣ ስለትምህርት የዓለም አቀፍ (EI) ---- ሌሎችም በትምህርትና በመምህራን ጉዳይ የተሰጡትን ትኩረቶች ለመጥቀስ ሞክረናል። ነገር ግን ወያኔ የነዚህን ግዙፍ ድርጅቶችንና ለጋሽ መንግሥታትን እይታ የሚጋርድ የፕሮፖጋንዳና የማደናገሪያ ስልት እየሰራ በመገኘቱ ዕውነታውን አደብዝዞታል።በዚያው ላይ ምዕራባውያን የራሳቸውን ጥቅም በማስቀደማቸው በሌሎች አገሮች ያሉ የሰራተኛና የሙያ ማህበራት ባጠቃላይ ሲቪል ማህበራት ለአገሮቻቸው ሊያበረክቱ የሚችሏቸውን በጎ ተግባራት ሁሉ እየተደናቀፉ ይገኛሉ። ለዚህ እንደምሳሌ የሚታየው ኢመማና አባላቱ የኢትዮጵያ መምህራን ናቸው። ቀደም ባሉት ዓመታት ትምህርት አለም አቀፍ (EI) ፣ የዓለም ሠራተኞች ማህበር (I.L.. O) እና ከላይ ስማቸው ከተጠቀሱት አንዳንድ የመምህራን ማህበራት ከኢመማ ጎን ቆመው የኢትዮጵያን መምህራን ከጭቆና ለማውጣት ብዙ ጥረት አድርገዋል። በተለይ የእንግሊዝ ብሔራዊ የመህራን ማህበር ( NUT) ፣ የአሜሪካ ብሔራዊ የመምህራን ህብረት( NEA) የኔዘርላንድ መምህራን ሕብረት (Duch Teachers Union (AOB))------ ያበረከቱት ሁለንተናዊ እገዛ በኢመማ ታሪክ የተመዘገበ ነው። በግለሰብ ደረጃ የእንግሊዙ ብሔራዊ የመምህራን ህብረት ዋና ፀሐፊ የነበሩት ስቲብሲኖት( Steve Sinnot) ፣ የኔዘርላንዱ አንድሬ ዱመንት (Andre  Dummont) ፣ በኢ. አይ የአፍሪካ ተወካይ ጋናዊው ቶም ባዲያኮ( Tom Bediako) ፣ የሴራሊዮኑ ኢማኑኤል ፋቶማ ( Emanuel Fatoma) ፣ ካናዳዊቷ ሺና ሐንሊይ ( Shenna Hanley) በህይወት ላሉትም ሆነ፣ በሞት ለተለዩት እንዲሁም በጡረታ ለተገለሉት ለሰሩት ውለታ  ምስጋናና አድናቆታችን እጅግ ከፍተኛ  ነው። በአሁኑ ጊዜ ያ ሁሉ ለእውነት መቆም ደብዝዟል ማለት ይቻላል።ኢመማ በነፃ ፍ/ቤት ሳይሆን በመንግሥት ትዕዛዝ በሚፈርዱ ዳኞች ፍርድ ተገምድሎበት ጽ/ቤቶቹ፣ በሚሊዮን የሚቆጠር የአባላቱ ገንዘብ ፣ እንጡራ ሀብቱንና መብቱን አጥቷል። ይህ ሁኔታ መለወጥ እንዳለበት ኢመማ በጽኑ ያምናል። እነዚህ ድርጅቶችም ሆኑ ለጋሽ መንግሥታት አውቀውም ሆነ ባለማወቅ ከእነዚህ አምባገነኖች ጎን ቆመው የማያልፈውን ሕዝብ በሚያልፍ መንግሥት የተሳሳተ አቅጣጫ አጃቢ እንዳይሆኑ እናሳስባለን።

ሰለዓለም መምህራን ቀን ኦክቶበር 5 ቀንጨብ አድርገን ለማሳየት ሞክረናል። በዚህ መግለጫ ርዕስ የኢትዮጵያ መምህራን ይህን ዓለም አቀፍ በዓል በነፃ ሕሊናና የወደፊት የትምህርቱ ሂደት በስኬት እንዲራመድ፣ የሙያ ክብራቸው የተጠበቀ ሆኖ ከሌሎች አገሮች የሙያ አገሮቻቸው ጋር በተለያዩ አጋጣሚዎች ግንኙነት በመፍጠር ልምድ የሚለዋወጡበት፣ ባጠቃላይ የማስተማር ሥራ ለሕብረተሰቡ የዕድገት መሰረት እንዲጥል ሁለንተናዊ ክህሎታቸውን አሟጠው የሚጠቀሙበት መንግሥታዊ ሥርዓት የሌለበት ወቅት በመሆኑ ኦክቶበር 5ትን በሰቀቀን አስበዉት እንዳሳለፉ ለማሳየት እንሞክራለን። የኢትዮጵያ መምህራንና ማህበራቸው ኢመማ ከወያኔ የሚወርድባቸውን የግፍ ዶፍ ሳያባራ አለንበት ወቅት ላይ ደርሰናል።ስቃይ ሰቆቃው ለመቀጠሉና ለሰጠነው ርዕስ  ዋቢ እንዲሆን ባንድ ት/ቤት ላይ ብቻ የተፈጸመውን ፍትህ አልባ ደባ ከዚህ ቀጥለን እናቀርባለን።

የእቴጌ መነን ት/ቤት በ1923 ዓ.ም በእቴጌ መነን አስፋው በጎ ፈቃድ ለኢትዮጵውያን ሴት ተማሪዎች መማሪያ ታስቦ የተመሰረት ሲሆን ከመንግሥት ለውጥ በኋላ ስያሜው " ያካቲት 12  ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት" በሚል ተለውጦ ከ1972 ዓ.ም ወዲህ ደግሞ ወንድና ሴት ተማሪዎችን በአንድነት በማስተማር ላይ የሚገኝ ብዙ ልምድና ችሎታ ያላቸው መምህራን የሚገኙበት አንጋፋ ት/ቤት ነው። ይህ አንጋፋ ት/ቤት በማተማርና መማር ሂደት አገርና ወገን የሚያኮሩ በርካታ ዜጎችን በማፍራት ተጎዞ እነሆ መስከረም 8/2008 ዓ.ም 85ኛ ልደቱ ላይ ደርሷል።

ትምህርት ቤቱ በሀገራችን ኢትዮጵያ ከሚገኙ ጥቂት ምርጥና ስመገናና ት/ቤቶች አንዱ ለመሆኑ በውስጡ ያለፉ ውጤታማ ተማሪዎችና አጠቃላይ ታሪኩ ሕያው ምስክሮች ናቸው።ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን ከሌሎች ት/ቤቶች በተለየ በመንግሥት ካድሬዎች ሆን ተብሎ በሚካሄድ የጥፋት እርምጃ ምርጥና አንጋፋ መምህራን ላይ የሚደርሰው ወከባና በደል ት/ቤቱ ከጊዜ ወደ ጊዜ ደረጃው እንዲያሽቆለቁልና ዝናው እንዲደበዝዝ ወደ መጨረሻ የውድቀቱ አዘቅትም እንዲወርድ እየተደረገ ይገኛል።

የካቲት 12 መሰናዶ ት/ቤት በአንፃራዊነቱ ሲታይ በልምድና በእውቀት የዳበሩ አንጋፋ መምህራን የሚገኙበት ቢሆንም ይህ ስዕል አገርንና ሕዝብ በማይወደው በወያኔ መንግስት ካድሬዎች አልተወደደም። ወያኔ/ኢህአዴግ እነዚህን መምህራን እንደስጋት ምንጭ በመቁጠር በዓይነ ቁራኛ የሚያይበት ምክንያት ቀጥሎ ያሉት የሚጠቀሱ ናቸው፡-

- መምህራኑ በትምህርት ጥራት ውድቀት ላይ የሚያሳዩት ተቆርቋሪነት ፣ ቁጭትና ከዚያም ባለፈ የተቃውሞ ድምፅ ሥርዓቱን ባለማስደሰቱ፣
- የወያኔ መንግስት ራሱ ለመምህራን በሚያዘጋጃቸው  አጀንዳዎች ላይ የሚሰጧቸው ገንቢ አስተያየቶች በካድሬዎቹ በኩል በአገዛዝ ለመቆየት እንጂ ለሕዝብና ለአገር ደንታ ቢስ ስለሆነ የመምህራኑ ሀሳብ ሰለማይዋጥላቸው፣
- ብቃት የሌላቸው የትምህርት ቤት የአስተዳደር አካላት የሚፈጽሙትን ብልሹ አሰራርና ሙስና በመጋለጣቸው፣
- 1 ለ 5 የወያኔ ትርኔፈ  እና ለመሳሰሉት የወያኔ ፖለቲካዊ አደራጃጀቶች የት/ቤቱ መምህራን ምቹ አለመሆናቸው ሊጠቀሱ  የሚችሉ ናቸው።

*ከላይ በተጠቀሱትና በመሳሰሉት ጉዳዮች ምክንያት በመህራን ላይ የሚደርሱ በደሎች ደግሞ፡-*

1. *በ2004 ዓ.ም ለመምህራን የተደረገው የደመወዝ ጭማሪ ከሰባ ብር( ብር 70) ያልበለጠ ሆኖ ሳለ የወያኔ/ኢህአዴግ መንግሥት በሚዲያ ባስተላለፈው እጅግ የተጋነነ መግለጫ የተበሳጩ ሁሉም ትምህርት ቤቱ መምህራን ለሶስት ቀናት የስራ ማቆም አድማ ያደረጉ ሲሆን የ27 መምህራንን ስም ዝርዝር በማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ በመለጠፍ ከባድ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷቸዋል።ድርጊቱ በዚህ ብቻ ሳያቆም እነዚህ መምህራን ማግኘት የሚገባቸውን የደረጃ ዕድገት፣ የትምህርት ዕድልና ሌሎች ጥቅማጥቅሞችን ተከልክለዋል። ይህም ወያኔ መምህራንን ከፈፍሎ የሚያጠቃበት ስልት ነው።*
2. *በ2007ዓ.ም በተደረገው አገራዊ የቦልት ምርጫ  ወቅት ረብሻ ያስነሳሉ የተቃዋሚ ፓርቲ አባላት ወይም ደጋፊ ሊሆኑ ይችላሉ ስለሆነም የመንግሥት ስጋት ናቸው በሚል ምክንያት አልባ ጥርጣሬ ምናልበት ረብሻ ቢነሳ በቁጥጥር ስር እንዲውሉ በማለት የአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን ለክፍለ ከተማውና ለወረዳው ፖሊስ ጣቢያዎች የትምህርት ቤቱን 20 መምህራን ስም ዝርዝር አስተላልፎ ነበር።በዚህም ምክንያት በመምህራኑ ላይ ስውር ክትትል ይደርግባቸው ነበር።*
3. *እንዳጋጣሚ ረብሻ ቢፈጠር እነዚህ መምህራን በሽብርተኝነት ተከሰው የአዳፍኔ ምስክር ተቆጥሮባቸው ፣ አቃባጭ ሕግ( አቃቤ ሕግ) የሐሰት የክስ ተውኔት አቅርቦ ዘብጥያ ይወርዱ እንደነበር መገመት አያዳግትም።ለነገሩ የተጠመደው ወጥመድ እንዳለ ስለቆየ ከነሐሴ 28ቀን 2007 ዓ.ም ጀምሮ ከ25 እስከ 30 ዓመታት ያገለገሉና  የትምህርት ደረጃቸው የመጀመሪያ ድግሪና ከዚያ በላይ የሆኑ መምህራንን ጨምሮ 25 መምህራን ከያካቲት 12 መሰናዶ ት/ቤት ወደ ሌላ ትምህርት ቤት ያለፍላጎታቸው እንዲዛወሩ ተገደዋል።*
4. *እንዲሁም ከምዕራፍ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት፣ ከመድኃኔዓለም 2ኛ ደረጃ ት/ቤት፣ ከእንጦጦ  አምባ 2ኛ ደረጃ ት/ቤትና ከድል በር 2ኛ ደረጃ ት/ቤት 15 መምህራን ያለፍላጎታቸው በግዳጅ ወደ ሌሎች ትምህርት ቤቶች እንዲዛወሩ ሆኗል።*

*በአንፃሩ ደግሞ የትምህርት ቤቱ  ኃላፊዎች የስራ ልምድ ከ6-8 ዓመት ብቻ የሆነና የትምህርት ደረጃቸውም ዲፕሎማና ድግሪ በሚል እውቅና ከሌላው ከድንጋይ ማምረቻ ተቋም ለመመረቃቸው ጥቆማ ብደርስም  ለማጣራት የደፈረ ፣ የፈለገም አካል አለመኖሩ ለት/ቤቱ ውድቀት መንደርደሪያ እንደሆነ እየተነገረ ነው። ከዚሁ ጋር ተያይዞ ያለፈው ዓመት (2007 ዓ.ም) የ12ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና መሰረቁ በሚዲያ ተነግሯል። ስርቆቱ የተካሄደው የተወሰነውን ክልል ለመጥቀምና ሌሎችን ለመጉዳት እንደሆነ ይታመናል። ድርጊቱም  የምዘናውን ሥርዓት የሚያዛባ ትልቅ በትምህርት ሂደት ላይ የተፈጸመ አቢይ ደባ ነዉ። ስርቆት ያካሄደው ግለሰብ ወይም ቡድን ተጠያቂ ያለመሆኑም በትምህርት ሥራ ፍትሐዊነት ላይ ያጠላው  አደጋ አንድ ማረጋገጫና ዋቢ ነው።*

*በሰደት የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር አባላት አስተባባሪ ኮሚቴ በየካቲት 12  መሰናዶ ት/ቤት መምህራንና በሌሎች ከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች መምህራን ላይ የተፈጸመውን የመብት ረገጠና ሕግ ወጥ ዝውውር፣ በትምህርቱ ዘርፍ ላይ የሚደረገውን ውድቀትና ስርቆት በጥብቅ ያውግዛል።*
*መብታቸውን ለማስከበር ከወራት በላይ የስራ ማቆም አድማ በማድረግና በፍርድ ቤትም ጭምር ጉዳያቸውን በማቅረብ የኬንያ መንግሥትን በማስጨናቅ ላይ እንደሚገኘው እንደ  ኬንያ መምህራን የኢትዮጵያ መምህራንም በስልት በመደራጀት መብትን ማስከበር የጊዜው ጥያቄ ነው  ። ወላጆች ፣ ተማሪዎች፣ ኣጠቃላይ ሕብረሰቡ አንድ ላይ በመሆን ይህ ግፈኛ የወያኔ መንግሥት በትምህርት ላይ የሚፈጽመው ወንጀል በስልትና በጥናት አገርንና ትውልዱን ለማጥቃት የሚያረምደው መጥፎ ተግባር መሆኑን በመገንዘብ በጋራ የስርዓት ለውጥ ለማምጠት  እንዲታገሉ በሰደት የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር አባላት አስተባባሪ ኮሚቴ በድጋሚ ጥሪውን ያቀርባል።  እንኳን ለኦክቶበር 5 የዓለም መምህራን ቀን አደረሰን።*

*ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!!*
*ኦክቶበር 5 የዓለም መምህራን ቀን ይለምልም!!*
*የመምህራን ስቃይ በትግል ያበቃል!!*